# ይድረስ ለብርቱዋ!!! ቁ. 4

ከከበቡሽ አየናቸው

በጤናሽ፣ በኑሮሽ፣ በመንፈስ ጽናትሽ፣
እንደምን ይዞሻል ብርቱዬ እንደምን ነሽ?
እኔም ባለሁበት መኖር እኖራለሁ፣
እንደተለመደው ተመስገን እላለሁ።
ብእሬ ባለፈው ሰላምታ ከጻፈ፣
ይኸው እንደዋዛ ሁለት ወር አለፈ።
ኑሮ አንበለውና ሳታምኝው ሳናምነው፣
የቃሊቲው ኑሮሽ ሦስት ወር አለፈው።
ትፈቻለሽ ብለን ስንጠብቅ በእምነት፣
ጥምቀትም አለፈ፣ ትንሣኤም አለፈ
ተስፋ የጣልንበት።
ቂሱም ዘም፣ መጽሐፉም፣ የዘንደሮው እምነት።
መቸስ ምን ይደረግ ታሪክ ሲንከባለል፣
ከአጋም የተጠጋ ቁልቁል አድርጎናል።
የእንመለስ ነገር አያደር ሲያዩዋቸው፣
በሚሠሩት ሁሉ የሚገርሙ ናቸው።
ሕሊና የላቸው፣ ወይ ህግ አይገዛቸው፣
አኒያ ታላቁ ሊቅ እንደ ገለጡዋቸው፣
በሕገ አራዊት የሚመሩ ናቸው።
እግዜርን አይፈሩ፣ ታሪክን አያፍሩ፣
መዝናኛቸው ሆኖአል ማሰደድ መሠሩ።
አኗዱ ትኩስ ወሬ በረድ ሲልባቸው፣
ሌላውን ለመፍጠር እንቅልፍም የላቸው።
’ብርቱካን ትፈታ!' የሚለው ሲበዛ፣
ሌሎችን ለማሠር በዋዛ ፈዛዛ፣
የፈጠራ ወንጀል ይታያል ሲነዛ።
በጥላሁን ለቅሶ የሕዝቡ ዕንባ ሳይደርቅ፣
አዲስ ወሬ ፈጥረው መጨነቅ፣ ማስጨነቅ።
ዛሬስ ብለው ብለው፣ ጠፍቶባቸው ውሉ፣
አንዱን ’ምርጥ ጀኔራል፣ ታግለው ያታገሉ፣’
ሊፈጅን ነበረ ፣ብለው ወነጀሉ።
የሚቀር ይመስል ሲበዛ በደሉ።
ወያኔ በሙሉ በጣም ተደናግጡዋል፤
ጥላውን፣ ቆሌውን ማመን አቅቶታል።
እነ ብርሃኑንም በጀግንነት አምቶአል።
እንደማይቀርለት የገባው የመሰላል።
ይገርምሻል ብርቱ የሚሠሩት ሥራ፣
ለማመን ያቅታል ይቀፍፋል ሲወራ።
አረጋዊው ቡልቻ የኦሮሞው መሪ፣
የፓርላማው አባል እውነትን መስካሪ፣
’ውንጀላው ይጣራ በገለልተኛ አካል፣
ተደጋጋሚ ነው ያጠራጥረናል፣’

